

## SDOT ለምንድነው የመንገድ ላይ መኪና ማቆሚያን የሚያስተዳድረው?

የመንገድ መኪና ማቆሚያን የምናስተዳድረው ትስስር ያላቸው ሰዎች፣ ቦታዎች፤ እና ምርቶች ያሉባትን ደማቅ ከተማ ለመደገፍ ነው።

ከመንገዱ ጐን ያለውን ክፍት ቦታ ለመኪና ማቆሚያ እንጠቀማለን፤ ነገርግን ለአውቶቡስ እና ለብስክሌት መስመር፣ ዕቃ ለሚያደርሱ፣ ለካፌ፤ እና ለሌሎች ነገሮችም እንጠቀመዋለን። ብዙ ሰዎች እና ንግዶች ይህንን ክፍት ቦታ ለመጠቀም ይፈልጋሉ፣ ግን ውስን ስለሆነ መጋራት ያስፈልገናል። ከተማችን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች መሰረት በማድረግ፣ ይህንን ክፍት ቦታ ለመጠቀም ከሁሉ ምርጥ ስለሆኑ መንገዶች ውሳኔ እናደርጋለን። ደህንነቱ በተጠበቀና ቅልጥፍና በተመላ ሁኔታ በሲያትል አካባቢ መዘዋወር እንዲችሉ እንፈልጋለን። እንዲሁም ለአየር ንብረት ግቦቻችን እየሰራን ንግዶችን እና ለኑሮ ምቹ ሠፈሮችን መደገፍ እንፈልጋለን።

**የመንገድ መኪና ማቆሚያን እንዴት እንደምናስተዳድር፡-**
ከኩርባ አጠገብ ያለውን ክፍት ቦታ ለማስተዳደር የተለያዩ መሳሪያዎችን እንጠቀማለን። የሚከፈልባቸው የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች እና የመጫኛ ዞኖች  በንግዶች አጠገብ የአጭር ጊዜ መዳረሻን የምንፈጥርባቸው ሁለት መንገዶች ናቸው። እና በአንዳንድ የመኖሪያ ሰፈሮች ውስጥ፣ በሆስፒታሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች ዋና ዋና ተቋማት አቅራቢያ ቀኑን ሙሉ የተመላላሽ የመኪና ማቆሚያ ለመቀነስ የተከለከለ የመኪና ማቆሚያ ዞኖችን (RPZs) እንፈጥራለን። ሰዎች እነዚህን ክፍት ቦታዎች እንደታቀደው መጠቀም እንዲችሉ ለማረጋገጥ፤ ከሲያትል ፖሊስ መምሪያ የመኪና ማቆሚያ ማስፈጸሚያ ቡድን እና ከሲያትል ማዘጋጃ ቤት ፍርድ ቤት ጋር አብረን እንሰራለን።

ጥያቄዎች ሲኖርዎት ወይም እርዳታ ሲፈልጉ እኛን የሚያገኙበት ብዙ መንገዶች አሉን። በዚህ የእጅ መጽሔት ውስጥ እርስዎ ጠቃሚ የግንኙነት መረጃ ያገኛሉ።

## የመኪና ማቆሚያ ቲኬቶች

የመኪና ማቆሚያ ትኬቶች እንደማያገኙ ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም ቲኬት ከተሰጥዎት፣ እርምጃ ለመውሰድ 15 ቀናት አለዎት። ክፍያ ለመፈጸም ብዙ አማራጮች አለዎት፦

### በፖስታ፣ በቀረበው መላኪያ ፖስታ ውስጥ

Municipal Court of Seattle
PO Box C-34109
Seattle, WA 98124-1109



**በስልክ፡**
(206) 233-7000

**በኢንተርኔት፦**
seattle.gov/courts/ ticket-and-payments/pay-my-ticket

### በአካል፦

- Municipal Court of Seattle፣ 600 5th Ave, ከሰኞ–ዓርብ፣ ከጠዋቱ 8 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት
- ከፍርድ ቤት ዋና መግቢያ ውጭ በስተቀኝ በኩል ደህንነቱ የተጠበቀ ማስቀመጫ ሳጥን
- የሲያትል የደምበኛ አገልግሎት ማዕከላት

### የፍርድ ቤት ችሎቶች

ቲኬቱ በስህተት ነው የተሰጠኝ ብለው ካመኑ እና ቲኬቱን በዳኛ ፊት መሟገት ከፈለጉ፣ የፍርድ ክርክር ያለበትን ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።

እርስዎ ጥሰቱን እንደፈጸሙ ከተስማሙ ግን በሁኔታዎች ምክንያት ቅጣቱን እንዲቀንስ ዳኛ መጠየቅ ከፈለጉ፤ ቅጣቱን ለማስቀነስ በችሎት እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ።

**ለበለጠ መረጃ፦**
(206) 684-5600 ወይም seattle.gov/courts/ tickets-and-payments/dispute-my-ticket

## የሚያስከፈሉ የመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ

የሚከፈልበት የመኪና ማቆሚያ በአጠቃላይ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ፤ ከጠዋቱ 8 ሰአት እስከ ምሽቱ 8 ሰአት ይሰራል። አንዳንድ ሰፈሮች እስከ ምሽቱ 10 ሰዓት ድረስ የሚከፈልበት የመኪና ማቆሚያ አላቸው፣ እና አንዳንድ ልዩ ዝግጅቶች ሲኖሩ እሁድ እና በዓመት በዓል ቀንም እንዲሁ የሚያስከፍል የመኪና ማቆሚያ ሊኖራቸው ይችላሉ። ሁልጊዜ በመንገድ ላይ ያሉትን ምልክቶች ያንብቡ። ዋጋዎች እና ሰዓቶች በዓመት ሦስት ጊዜ ይስተካከላሉ እና እንደየአካባቢው ሁኔታ ላይ ይለያያሉ። ብዙ የተጨናነቁ መንገዶች በጠዋት እና በምሽት ጉዞዎች ወቅት የመንገድ መኪና ማቆሚያ ገደቦች አሏቸው።




የስልክ ክፍያ እና የክፍያ ጣቢያ ኪዮስኮች በሁሉም የመኪና ማቆሚያ የሚከፈልባቸው ቦታዎች ይገኛሉ። መተግበሪያውን ከአፕ ስቶርዎ ያውርዱና ለፈጣን እና ምቹ የመኪና ማቆሚያ መክፈያ ያዘጋጁ።

## መገናኛ እና መረጃዎች

**ለበለጠ መረጃ፦**
(206) 684-7623

**ድንገተኛ ላልሆኑ ሁኔታዎች የመኪና ማቆሚያ አስከባሪ መኮንን ለመጥራት፦** (206) 625-5011፣ አማራጭ #6

**የተጣሉ ተሽከርካሪዎችን ሪፖርት ለማድረግ:**
Find It, Fix It (አግኝ፣ አስተካክል) መተግበሪያ ይጠቀሙ ወይም በ(206) 684-8763 ይደውሉ

**መኪናዎ ከህዝብ መንገድ ተጐትቶ ከሆነ:** (206) 364-2000 ወይም ወደ seattleimpound.com ይሂዱ

**ለSDOT የመኪና ማቆሚያ መረጃ፣ ነጻ የመኪና ማቆሚያ ቀናትን ጭምር፣ የተከፈለ የመኪና ማቆሚያ ተመኖች እና ካርታዎች:** seattle.gov/parking

**ለስማርት ስልክ ለተዘጋጀ የዳውንታውን የመኪና ማቆሚያ ካርታ፦** DowntownSeattleParking.com



## ያልተከፈሉ ቲኬቶች

አራት እና ከዚያ በላይ ያልተከፈሉ የመኪና ማቆሚያ ቲኬቶች ያላቸው ተሽከርካሪዎች ጐማቸው ይጠፈራል። አንዴ ጎማው ከተጠፈረ፣ ቲኬቶች እና ሌሎች ክፍያዎች በ48 ሰአታት ውስጥ ካልተከፈሉ በስተቀር፣ ተሽከርካሪው ተጎትቶ ይወሰዳል።

**ተጨማሪ መረጃ በ፦**
seattle.gov/courts/tickets-and-payments/my-car-got-booted

AMHARIC

# እዚህ መኪና ማቆም እችላለሁ?



## ምልክቶቹን ይመልከቱ እና ቲኬት ማግኘትን ያስወግዱ

## እንዴት እንደሚሰራ እናሳይዎታለን

Seattle Department of Transportation

9.2025

# መኪና ማቆም አይፈቀድም

## የውስጥ ለውስጥ/የጓሮ መንገዶች

በውስጥ ለውስጥ/የጓሮ መንገዶች ላይ መኪና አያቁሙ። የንግድ ተሽከርካሪዎች እስከ 30 ደቂቃ ድረስ ሊጭኑ/ሊያወርዱ ይችላሉ።

## ማቆም እና ቅድሚያ መስጠት

ከማቆሚያ እና ከቅድሚያ መስጫ ምልክቶች በ30 ጫማ ርቀት ውስጥ አያቁሙ፣ እንዲሁም ከእግረኛ ማቋረጫ መንገድ በ20 ጫማ ርቀት ውስጥ አያቁሙ።

## ወደ ቤት መግቢያ የመኪና መንገዶች

ወደ ቤት ከመግቢያ የመኪና መንገድ 5 ጫማ ርቀት ውስጥ መኪና አያቁሙ። ወደ ቤት መግቢያ የመኪና መንገድ 5 ጫማ ርቀት በእያንዳንዱ ጎን ነዋሪዎች/ የቤት ባለቤቶች ኩርባውን ቢጫ መቀባት ይችላሉ።

## የእሳት ማጥፊያ የመንገድ ዳር ቧንቧዎች

ከእሳት ማጥፊያ በ15 ጫማ ርቀት ውስጥ አያቁሙ።

## የእግረኛ መንገዶች እና የመንገድ ዳር የዕጽዋት መትከያ ቦታዎች

በእግረኛ መሄጃ ላይ ወይም በእግረኛ መሄጃ እና በመንገዱ መካከል ያለው የዕጽዋት መትከያ ቦታ ላይ አያቁሙ።

## መስቀለኛ መገናኛዎች እና የእግረኛ ማቋረጫዎች

በመስቀለኛ መንገድ ወይም በእግረኛ ማቋረጫ፣ ወይም መስቀለኛ የ"T" መገናኛዎችን ጨምሮ፣ በ20 ጫማ ርቀት ውስጥ መኪና አያቁሙ። መኪና ማቆም አይቻልም የሚሉ ምልክቶች እንዳሉ ያረጋግጡ። የእግረኛ ማቋረጫዎች ምልክት ሊደረግባቸው (በቀለም ቅብ) ወይም ላይደረግባቸው (ምንም የቀለም ቅብ) ይችላል።




## መኪና የሚጎተትባቸው ዞኖች

በእነዚህ ዞኖች ውስጥ ወይም በማንኛቸውም ቀይ የተቀቡ ዞኖች ውስጥ አያቁሙ።



## መኪና ማቆም የማይቻልበት ዞኖች

በእነዚህ ዞኖች ውስጥ መኪና አያቁሙ።




## ጊዜያዊ መኪና ማቆም የማይቻልበት ዞኖች

በተለጠፉት ቀናት እና ሰዓቶች ወቅት እዚህ መኪና አያቁሙ። ለጥያቄዎች፣ በ(206) 684-7623 ይደውሉ።


## ሌሎች የተሰየሙ ዞኖች

ለአውቶቡሶች፣ ለታክሲዎች፣ ለቻርተር አውቶቡሶች፣ ለካርሼር ተሽከርካሪዎች፣ ወይም በሰያፍ ምልክት የተደረገባቸው የመንገድ ዳር ቦታዎች ላይ አያቁሙ።

## የንግድ እና ትላልቅ ተሽከርካሪዎች

የኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር፣ ከእኩለ ሌሊት እስከ ጠዋቱ 6 ሰዓት ድረስ ከ80 ኢንች በላይ ስፋት ያለውን ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ወይም የውስጥ ለውስጥ/የጓሮ መንገድ ላይ አያቁሙ።

## ምን ያህል ተጠግቼ ማቆም እችላለሁ?




# መኪና ማቆም አንዳንዴ ይፈቀዳል





## ለአካል ጉዳተኞች መኪና ማቆሚያ

1) እርስዎ ወይም ተሳፋሪዎ አካል ጉዳተኛ ካልሆነ በስተቀር፣ እና 2) ተሽከርካሪዎ ትክክለኛ የአካል ጉዳተኛ የሚንጠለጠል ካርድ፣ ታርጋ ወይም ታብ ካላሳየ በስተቀር በተሰየመ የአካል ጉዳተኛ ፓርኪንግ ውስጥ አያቁሙ ወይም ፍቃድ አይጠቀሙ። አላግባብ ከተቀመ ቅጣቱ እስከ $450 ዶላር ነው።




## የምግብ ተሽከርካሪ ዞኖች

በ"የምግብ ተሽከርካሪ ዞን" ስር በተለጠፉት ሰዓታት የተፈቀዱ የምግብ መኪናዎች ብቻ ማቆም ይችላሉ። ሌሎች ከእነዚያ ሰዓታት ውጭ መኪና ማቆም ይችላሉ፣ ነገር ግን በ"ክፍያ ጣቢያ ጋ ይክፈሉ" በሚለው ስር እንደተለጠፈው ክፍያ ሊያስፈልግ ይችላል።




## ገደብ ያላቸው የመኪና ማቆሚያ ዞኖች (RPZ)

ተሽከርካሪዎ የRPZ ፈቃድ ካለው፣ የRPZ ምልክት የተደረገባቸው መንገዶች ላይ እስከ 72 ሰአታት ድረስ መኪና ማቆም ይችላሉ። ካልሆነ፣ እርስዎ በተለጠፈው ጊዜ ብቻ መገደብ አለብዎት፡ ይደውሉ፡-(206) 684-5086።




## የጭንቅንቅ ሰዓቶች

በተለጠፉት ጊዜያት መኪና አያቁሙ፣ አለበለዚያ ተሽከርካሪዎ ይጎተታል። የተከለከሉ ሰዓቶች ስለሚለያዩ ምልክቶችን በጥንቃቄ ያረጋግጡ።





## በጊዜ-የተገደቡ ቦታዎች

እስከ ተለጠፈው የጊዜ ገደብ ድረስ መኪና ያቁሙ። ከዚያ በኋላ ተሽከርካሪዎ ከብሎኩ ላይ ማንሳት አለብዎት (ከመንገዱ በሁለቱም በኩል)፡- ለምሳሌ፣ ወደ ቀጣዩ ብሎክ ወይም መንገዱን ዞር ብሎ።




## መጫኛ እና ማውረጃ

ሁሉም ተሽከርካሪዎች በተለጠፈ ሰአት ወቅት መጫን/ማውረድ ይችላሉ። (የኩርባ ቀለም፦- ቢጫ)





## ተሳፋሪ መጫን

በተለጠፈ ሰአታት ወቅት ተሽከርካሪዎች ሁሉ ተሳፋሪዎችን ለማንሳት እና ለማውረድ ለ3 ደቂቃ ያህል መቆም ይችላሉ። (የኩርባ ቀለም፦- ነጭ)




## የከባድ መኪና መጫን እና ማውረድ

የጭነት መኪና ፍቃድ የተሰጣቸው ተሽከርካሪዎች ብቻ ናቸው በተለጠፈ ሰአት መጫን/ማውረድ የሚችሉት። (የኩርባ ቀለም፦- ቢጫ)




## የንግድ ተሽከርካሪ መጫኛ ዞኖች (CVLZ)

እስከ 30 ደቂቃ ድረስ መጫን/ጭነት ማውረድ የሚችሉት የንግድ ተሽከርካሪዎች ብቻ ናቸው። ወይ ክፍያ ወይ የሚሰራ CVLZ ፈቃድ ያስፈልጋል። ይደውሉ፦-(206) 684-5103 (የኩርባ ቀለም፦- ቢጫ።)

## ሌሎች ሁኔታዎች

**የመኪና ታርጋ ሰሌዳዎች እና ታቦች**

የፊት ወይም የኋላ ሰሌዳዎች የጎደሏቸው፣ ወይም ጊዜው ያለፈባቸው ታብ ያሏቸው የቆሙ ተሽከርካሪዎች ቲኬት ሊሰጣቸው ይችላል።

**የ72-ሰዓት ደንብ**

ተሽከርካሪዎን በአንድ ብሎክ ላይ ከ72 ተከታታይ ሰአታት በላይ አያቁሙ፣ አለበለዚያ ተሽከርካሪው እንደተተወ/ እንደተጣለ ይቆጠርና ቲኬት ሊሰጠው ወይም ሊጎተት ይችላል።